በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር 1.0/557/08
Ref. No.
ቀን 22 ግንቦት 2008
Date

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ

በያሉበት

ጉዳዩ፡ የጸደቀ መመሪያ ስለመላክ፤

የቱሪስት መገልገያ ዕቃዎች በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 116/2008 ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ በማድረግ የላክንላችሁ ስለሆነ መመሪያው ተግባራዊ እንዲደረግ አሳስባለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

አብርሃም ንጉሴ
ተ/ዋና ዳይሬክተር

ግልባጭ፤

- ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለሕግ ማስከበር ስራዎች ዘርፍ
- አገር ውስጥ ታክስ ፕሮግራም፣ ልማትና ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ
- ለጉምሩክ ፕሮግራም፣ ልማትና ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ
- ለሞደርናይዜሽንና ኮርፖሬት ስራዎች ዘርፍ
- ለአዲስ አበባ ታክስ ፕሮግራም፣ልማትና ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ
- ለህግ ጥናት፣ ረቂቅና ዝግጅት ስልጠና ዳይሬክቶሬት
  ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ለዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንስራለን!!

ስልክ ቁ / Tel. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ/ Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ. / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ- ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

ዳይሬክቶሬት

- ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ አሰራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለየታክስ ህግ ተገዥነት ስጋት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ጉዳይ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለገቢ ሂሳቦች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለወንጀል ምርመራ ዳይሬክቶሬት
- ለዐቃቤ ሕግ ቢሮ
- ለአ.አ. ወንጀልና ፍትሐብሄር ጉዳዮች ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለፌዴራል ወንጀልና ፍትሐብሄር ጉዳዮች ክትትል ዳይሬክቶት
- ለህግ ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት
- ለህግ ምክርና አስተያየት ዳይሬክቶሬት
- ለኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት
- ለድንበር አስተዳደርና ኮንትሮባንድ ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለመረጃ ቴክኖሎጂ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለዕቅድና አፈጻጸም ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለንብረት አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለየተያዙና የተወረሱ ንብረቶች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለጥናትና ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለአገር ውስጥ ታክስ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ መረጃ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለኢንቨስትመንት ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ኦዲት አሰራር ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለግብር አወሳሰንና አሰባሰብ አሰራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለግዥና ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለሰው ሀብት ስራ አመራርና ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለለውጥ ትግበራ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለክልሎች ድጋፍና ትብብር ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለአዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለሴቶች ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት
- ለትምህርትና ኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
- ለውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለኢንቨስትጌሽን ኦዲት የስራ ሂደት
- ድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ፕሮግራም ልማት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለሥነ-ምግባር መከታተያ ዳይሬክቶሬት
- ለህብት አስተዳደር ቢሮ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

<u>ቅ/ጽ/ቤቶች</u>

- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለምዕራብ አዲስ አበባ መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለምስራቅ አዲስ አበባ መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለመርካቶ ቁጥር 1 መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- መርካቶ ቁጥር 2 መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቁጥር 1 መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቁጥር 2 መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለቦሌ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለቂርቆስ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለአራዳ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለየካ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለልደታ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለጉለሌ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- አዲስ ከተማ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

<u>አዲስ አበባ</u>

- ለአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት /<u>አዳማ</u>/
- ለሞጆ ቅ/ጽ/ቤት /<u>ሞጆ</u>/
- ለባህርዳር ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /<u>ባህርዳር</u>/
- ለመቀሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /<u>መቀሌ</u>/
- ለድሬደዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /<u>ድሬደዋ</u>/
- ለሚሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /<u>ሚሌ</u>/
- ለጅግጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /<u>ጅግጅጋ</u>/
- ለሞያሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /<u>ሞያሌ</u>/
- ለጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /<u>ጅማ</u>/
- ለጋላፊ ቅ/ጽ/ቤት /<u>ጋላፊ</u>/
- ለኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት /<u>ኮምቦልቻ</u>/
- ሐዋሳ ቅ/ጽ/ቤት /<u>ሐዋሳ</u>/

# የቱሪስት መገልገያ ዕቃዎችበጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ

## ቁጥር 116/08

ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
2008 ዓ.ም

# የቱሪስት መገልገያ ዕቃዎች በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ

የአገራችን የቱሪዝም ኢንደስትሪ ለአገራችን የገጽታ ግንባታ እና ለኢኮኖሚው ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋፆ ለማሳደግ እንዲቻል ለቱሪስት አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎች በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታና ዕቃዎቹን በጊዜያዊነት የሚያስገቡት ሰዎች የሚኖራቸውን መብትና ግዴታ የሚወሰን ዝርዝር አፈጻጸም መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ፣

ቱሪስቶች በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ በሚያስገቧቸው ዕቃዎች ላይ ውጤታማ ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል ግልጽና ወጥ አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 71/1/ እና 180/2/ መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የቱሪስት መገልገያ ዕቃዎች በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 116/08" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) "ቱሪስት" ማለት ወደ ኢትዮጵያ ግዛት መግባት የሚያስችል ፈቃድ/ቪዛ ያለው ወይም የኢትዮጵያ መንግሥት ባደረገው ስምምነት ወይም በህግ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ለመግባት የሚፈቀድለት፣አህጉራዊ ወይም ዓለም አቀፋዊ ጉባኤዎችን ወይም ስብሰባዎችን ለመሳተፍ ወይም ለጉብኝት ኢትዮጵያ የሚገባ እና በኢትዮጵያ ውስጥ ስራ የማይሰራ የውጭ አገር ዜጋ ሲሆን የውጭ አገር ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ ያለው ኢትዮጵያዊን ይጨምራል፡፡
2) "ቪዛ" ማለት ለጉብኝት ወደ ኢትዮጵያ ለሚመጡ ሰዎች የሚሰጥ የቱሪስት ቪዛ ሲሆን አህጉራዊ ወይም አለማቀፋዊ ጉባኤዎችን ወይም ስብሰባዎችን ለሚሳተፉ ሰዎች የሚሰጥ ቪዛን ይጨምራል፡፡
3) "የውጭ አገር ዜጋ" ማለት ኢትዮጵያዊ ዜግነት የሌለው ሌላ አገር ዜጋ ነው፡፡
4) "የቱሪስት መገልገያ ዕቃ" ማለት ቱሪስቱ የሚገለገልበት በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ገብቶ በተወሰነ ጊዜ ገደብ ውስጥ ተመልሶ የሚወጣ ዕቃ ሲሆን ተሽከርካሪን

5) "ተሽከርካሪ" ማለት የደረቅና የፈሳሽ ጭነት ተሽከርካሪን ሳይጨምር በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀስ ሰውን ለማጓጓዝ የሚያገለግል ተሽከርካሪ ሲሆን ሞተር ባይስክል እና ብስክሌትን ይጨምራል፡፡
6) "አዋጅ" ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ነው፡፡
7) "ባለስልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ነው፡፡
8) ሌሎች ቃላቶችና ሐረጐች በአዋጅ የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ቱሪስቶች በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ በሚያስገቧቸው ዕቃዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 4. ቅድመ ሁኔታ

ማንኛውም ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ቱሪስት ከዚህ በታች የተመለከተቱትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ይኖርበታል፤

1) ፓስፖርት፣
2) ከመጣበት አገር ወይም አገር ውስጥ ሲደርስ የሚሰጥ የቱሪስት ቪዛ፣
3) ኢትዮጵያዊ ለሆነ ቱሪስት ከመጣበት አገር ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ ያለው መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ፣
4) ቪዛ የማይሰጥበት ሀገር ከሆነ ከኢምግሬሽን የሚሰጥ የይለፍ ወይም መግቢያ ፈቃድ፣
5) በጊዜያዊነት ይዞት ለሚገባው ዕቃ ዋስትና፣
6) ተሽከርካሪ ይዞ የሚገባ ከሆነ ከመጣበት አገር ተሽከርካሪው ከአገር እንዲወጣ የተፈቀደበት ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም ቱሪስቱ በውጭ አገር የሚኖር ኢትዮጵያዊ ከሆነ ቪዛ እንዲያቀርብ አይጠየቅም፡፡

## ክፍል ሁለት

## የቱሪስቱመብትና ግዴታ

## 5. መብት

1) በዚህ መመሪያ መሰረት የቱሪስት ዕቃዎችን በጊዜያዊነት የሚያስገባ ማንኛውም ሰው፡-
   ሀ/ በጊዜያዊነት የሚያስገባቸውን ዕቃዎች በራሱ ወይም በወኪሉ አማካኝነት ወደ አገር ማስገባት ወይም ማስወጣት ይችላል፡፡
   ለ/ በጉምሩክ ህግ ለመንገደኞች ከቀረጥ ነጻ የሚፈቀደውን የግል መገልገያ ዕቃ ማስገባት ይችላል፡፡

ሐ/ የሚወጣበትን ጣቢያ መቀየር የፈለገ እንደሆነ አስቀድሞ ለድንበር አስተዳደርና የኮንትሮባንድ ክትትል ዳይሬክቶሬት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ወይም ለገባበት ጣቢያ በማሳወቅ ፈቃድ ማግኘት ይችላል፡፡

መ/ የተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ካለቀ በኋላ የማራዘሚያ ጊዜ ከሚመለከተው አካል የተሰጠው ከሆነ ለባለስልጣኑ የድንበር አስተዳደርና የኮንትሮባንድ ክትትል ዳይሬክቶሬት ወይም ቅ/ጽ/ቤትወይም መውጫ ጣቢያ ወዲያውኑ ማራዘሚያውን በማቅረብ በተራዘመው የጊዜ ገደብ ውስጥ ዕቃዎችን አገር ውስጥ ማቆየት ይችላል፡፡

2) ማንኛውም ቱሪስት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተዘረዘሩት መብቶች በተጨማሪ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፤-

ሀ/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 ተራ ፊደል ቸ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ ተደርጎ በተያያዘው ሰንጠረዥ የተዘረዘሩትን ዕቃዎች ወደ አገርማስገባት፣

ለ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል ሀ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች ለቱሪስት አገልግሎት የሚሆኑ ዕቃዎችን በጊዚያዊነት እንዲያስገባ በባለስልጣኑ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

ሐ/ በጊዜያዊነት ያስገባውን ዕቃ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ በማጋጠሙ ምክንያት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከአገር ለማስወጣት ካልቻለ ለባለስልጣኑ በማሳወቅ በአገሩ ኢምባሲ ቅጥር ግቢ ውስጥ ማስቀመጥ ወይም ለህጋዊ ወኪሉ በማስረከብ ወይም ባለስልጣኑ በሚፈቅደዉ ማናቸዉም ሌላ ቦታ ማቆየት ይችላል፡፡

## 6. ግዴታ

1) በዚህ መመሪያ መሰረት የቱሪስት ዕቃዎችን በጊዜያዊነት የሚያስገባ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ/ ዕቃ ይዞ ወደ አገር ሲገባ በመግቢያ ጣቢያ ዲክላሬሽን መሙላት እና የመግቢያ ፈቃድ ማግኘት፣ ፈቃዱንም በሚዘዋወርበት ቦታ ሁሉ ይዞ የመገኘት እና ሲጠየቅም የማሳየት፣

ለ/ ላስገባቸው ዕቃዎች የተፈቀደው የቆይታ ጊዜ ካልተራዘመለት በስተቀርዕቃውን በመጣበት አኳኋንና የጊዜ ገደብ ውስጥ የማስወጣት፣

ሐ/ ለሚያስገባው ዕቃበዚህ መመሪያ በተወሰነው ዓይነት ዋስትና ማቅረብ፣

መ/ ያስገባው ተሽከርካሪ ከዲክላራሲዮን እና ከሌሎች ሰነዶች ጋር ማገናዘብ እንዲቻል የውጭ አገር ዜጋስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ፓስፖርት፣ በመግቢያ ጣቢያ የተሞላ ዲክላራሲዮን ወይም የመሳሰሉትን ሰነዶች መያዝ እና በህግ አስከባሪዎች ሲጠየቅም የማሳየት፣

ሠ/ ዕቃ ያስገባ ከሆነ ለመግቢያ ጣቢያ ዕቃ ተመልሶ የሚወጣበትን ጣቢያ የማሳወቅ፣

ረ/ ባስገባቸው ዕቃዎች ላይ ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ጉዳት ሲደርስ በአቅራቢያው ለሚገኝ ፓሊስ ጣቢያ፣ የጉምሩክ ጣቢያ ወይም አስተዳደር ጽ/ቤት ሪፓርት በማድረግ የፅሁፍ ማስረጃ ለሚመለከተው የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ወይም ለድንበር አስተዳደርና የኮንትሮባንድ ክትትል ዳይሬክቶሬት በሁለት የስራ ቀናት ውስጥ የማቅረብ፣

ሰ/ በተሽከርካሪው ላይ ጉዳት ደርሶበት በጥገና ሊስተካከል የማይችልና መቀየር ያለበት ሆኖ ሲገኝ ስለዕቃዉ ብልሽት ፈቃድ ካለዉ ጋራዥ ማስረጃ በማቅረብ ዕቃውን ለመቀየር በአቅራቢያው ለሚገኝ ቅ/ጽ/ቤት የጉምሩክ ጉዳዮች ም/ስራ አስኪያጅ ወይም ለድንበር አስተዳደርና የኮንትሮባንድ ክትትል ዳይሬክቶሬት ፈቃድ የመጠየቅ፣

ሸ/ በዚህ አንቀጽ ተራ ፊደል ሰመሰረት የተቀየረውን የተሽከርካሪ አካል ዕቃ ተመልሶ እንዲወጣ በተወሰነላቸው ጊዜ ውስጥ ከአገር የማስወጣት፣

ቀ/ ከአገር ተመልሶ ለመውጣት ሲፈልግ በአገር ውስጥ ለመቆየት በተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ውስጥ በመውጫ በር በሚገኝ የጉምሩክ ጽ/ቤት በመቅረብ አስፈላጊውን የመውጫየጉምሩክ ስነ ስርዓት የመፈጸም፣

በ/ ከአገር ሲወጣ በጉምሩክ መውጫ በሮች ዲክላሬሽን የማሳየት፣

ተ/ ማንኛውም በአገሪቱም ሆነ አገሪቷ ባጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ክልከላ የተደረገባቸው ዕቃዎችን ይዞ ያለመግባት፣

ቸ/ ገደብ የተደረገባቸውን ዕቃዎች ይዞ ለመግባት ከሚመለከተው የተቆጣጣሪ መ/ቤት ፈቃድ የማቅረብ፣

ነ/ ዕቃዎቹ አገር ውስጥ እንዲቀሩ ሲወሰን ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ከሆነ ቀረጥና ታክሱን የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡

2) በዚህ መመሪያ መሰረት የቱሪስት ዕቃ በጊዚያዊነት ይዞ የገባ ማንኛውም ሰው ዕቃው ተመልሶ የሚወጣበትን የጉምሩክ ጣቢያ አስቀድሞ ያላሳወቀ እንደሆነ ዕቃው በገባበት ጣቢያ እንደሚወጣይገመታል፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Revenues and Customs Authority

## ክፍል ሦስት
## የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ኃላፊነትና ተግባር

### 7. የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶችና ጣቢያዎች ኃላፊነትና ተግባር

1) ቅ/ጽ/ቤቶች ወይም ጣቢያዎች በዚህ መመሪያ መሰረት በጊዜያዊነት ዕቃ ይዞ የሚገባን ሰው በተመለከተ የሚከተሉት ኃላፊነቶችና ተግባራት ይኖሯቸዋል፡-

ሀ/ ዕቃው ወደ አገር ሲገባና ከአገር ሲወጣ በጉምሩክ መግቢያና መውጫ በሮች በሲስተም ላይ ወይም በማንዋል የዕቃ ዲክለራስዮን እንዲሞላ እና ተገቢው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት እንዲፈፀም ማድረግ አለበት፣

ለ/ በመግቢያ በር የሚገኘው የጉምሩክ ጽ/ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በዕቃ ዲክለራስዮን የሞላው መረጃ ትክክለኛነት ከኦሪጅናል ሰነዶችና ከዕቃው አካላዊ ዕይታ ጋር በማመሳከር ዕቃውን ለማስገባት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች መሟላታቸውን አረጋግጦ በቅፁ ለፅህፈት ቤት አገልግሎት በተወሰነው ቦታ ላይ መስፈር ያለባቸውን ማረጋገጫዎች ማስፈር አለበት፣

ሐ/ በጊዜያዊነት የገባው ሰው በመጀመሪያ በገባበት በር ዕቃውን ሙሉ በሙሉ ይዞ ያልገባና ቀሪ ዕቃው በሌላ በር ወይም በተመሳሳይ በር በሌላ ጊዜ የመጣ ከሆነ ዕቃው የገባበት የጉምሩክ ጽ/ቤት ቱሪስቱ ሲገባ ዲክሌር ያደረገበትን፣ የዕቃ ዲክለራስዮን ተቀብሎ በአዲስ የዕቃ ዲክለራስዮን መረጃዎችን በማወራረስ አገልግሎት መስጠት አለበት፣

መ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሐ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የጊዜያዊነት የገባው ሰው በመጀመሪያ በገባበት በርምንም ዕቃ ይዞ ያልገባ ሆኖ ዕቃው በሌላ ወይም በተመሳሳይ በር የገባ ከሆነ ዕቃው የገባበት የጉምሩክ ጽ/ቤት የዕቃ ዲክለራስዮን እንዲሞላ አለበት፣

ሠ/ በጊዜያዊነት ከሚገባው ተሽከርካሪ ጋር በተያያዘ ለተሽከርካሪ ጥገና ለማድረግ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች፣ መለዋወጫዎች፣ቅያሪ ጐማና ከተሽከርካሪው የነዳጅ መያገዣ ታንከር ውጪ በትርፍነት /በሪዘርቭነት/ የተያዘ ነዳጅ እና የመሳሰሉት ወይም ከተሽከርካሪው መደበኛ ገጽታ (feature) ውጪ ለጌጥ ወይም ለተጨማሪ አገልግሎት የተገጠመ አካል ካለና ከፍተኛ ዋጋ ካለው ወይም ዕቃ ለመደበቅ ሊውል ይችላል ተብሎ ከተገመተ በዕቃ ዲክለራስዮን ላይ መሙላት አለበት፣

ረ/ በመውጫ በር የሚገኝ የጉምሩክ ጽ/ቤትም በጊዜያዊነት ዕቃ የሚያስገባው ሰው በመግቢያ ጉምሩክ ጽ/ቤት የተሰጠውን የገቢ ዕቃ ዲክለራስዮን ሲያቀርብ ይዞ የሚወጣውን ዕቃ እና የባለቤትነት/የውክልና ማስረጃ ትክክለኛነት በዕቃ ዲክለራስዮን ላይ ከሠፈሩ መረጃዎች/መግለጫዎች ጋር እንዲሁም ሌሎች ማስረጃዎች ጋር በማመሳከር እና ትክክለኛነቱን የዕቃ ዲክለራስዮን ላይ ለመውጫ የጉምሩክ ጽ/ቤት አገልግሎት

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Revenues and Customs Authority

በተመለከተው ቦታ ላይ በማረጋገጥ እራሱ ወይም ወኪሉ ዕቃዎቹን ይዞ እንዲወጣ ይፈቅዳል፤ የዕቃ ዲክላራሲዮንም በመቀበል ኦዲት እስኪደረግ ድረስ በጽህፈት ቤት ፋይል አድርጎ መያዝ አለበት፣

ሰ/ በጊዜያዊነት ዕቃ ይዞ የገባው ሰው በአገር ውስጥ የገዛቸው የግል መገልገያዎች የተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤት ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው ሆኖ ሲገኝ የጉምሩክ መውጫ ጣቢያ ከተቆጣጣሪው መ/ቤት ፈቃድ መቅረቡን ማረጋገጥ አለበት፣

ሸ/ በጊዜያዊነት ዕቃ ያስገባ ሰው ወደ አገር ሲገባ ያስገባቸውንና በጉዞ የሚጠቀምባቸውን እንደ ነዳጅ ያሉ ምርቶች በዚህ አንቀፅንዑስ አንቀጽ 1 ሠ ላይ ከተመዘገበው መጠን በላይ አለመያዙን ማረጋገጥ፣ ሆኖም መጠኑ በተሽከርካሪው የነደጅ መያዣ/ታንከር/ ያለውን አይጨምርም።

ቀ/ በጊዜያዊነት ዕቃ ያስገባ ሰው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1/መ/ መሰረት የጊዜ ማራዘሚያ የተፈቀደለት መሆኑን ማረጋገጫ ሲያቀርብ የዕቃውን መውጫ ጊዜ በተፈቀደው መጠን ማራዘም ይችላል፣

በ/ የድንበር አስተዳደርና የኮንትሮባንድ ክትትል ዳይሬክቶሬት በሰጠው ማስረጃ መሰረት በሌላ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ገብተው በሌላ በር የወጡ እንዲሁም በሌላ በር ገብተው በጣቢያ የሚወጡ ዕቃዎችን ፋይል አድርጎ መያዝ አለበት፣

ተ/ የተቆጣጣሪ መስሪያ ቤት ፈቃድ የሚያስፈልጋቸውን ዕቃዎች ይዞ በመምጣቱ በመግቢያ በሮች ላይ ፈቃድ መስጠት የማይቻል ሆኖ ሲገኝ የመግቢያ በሩ ጣቢያ ዕቃዎችን በአጃቢ ፈቃድ ወደሚሰጥበት አካባቢ ለሚገኝ የጉምሩክ ጣቢያ በማስተላለፍ ፈቃድ ሲገኝ ዕቃው እንዲለቀቅ ማድረግ አለበት።

2) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሠ) አፈጻጸም "ከፍተኛ ዋጋ" የሚባለው ከብር 10,000/አስር ሺህ ብር/ በላይ የሆነ ዋጋ ነው።

## 8. የድንበር አስተዳደርና የኮንትሮባንድ ክትትልዳይሬክቶሬት ኃላፊነትና ተግባር

ዳይሬክቶሬቱ የሚከተሉት ኃላፊነቶችና ተግባራት ይኖሩታል፦

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1/መ/ መሰረት በጊዜያዊነት የቱሪስትዕቃ ያስገባው ሰው የጊዜ ማራዘሚያ የተፈቀደለት መሆኑን ማረጋገጫ ሲቀርብለት ይመዘግባል፣ ለገባበት ቅ/ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ የተፈቀደው ጊዜ የተራዘመ መሆኑን ማሳወቅ ይኖርበታል።

2) የሚያስተናግዳቸውን ጉዳዮች እና የሰጠውን አገልግሎት በአባሪ በተያያዘው ቅጽ መሰረት በኮምፒውተር መዝገቦ በመያዝ በዚህ መመሪያ አንቀጽ (9) በተጠቀሰው መሰረት ይፈጽማል።

3) ከመግቢያና መውጫ በሮች የሚደርሱትን መረጃዎች እንዲሁም በራሱ በኩል የሰጣቸውን አገልግሎቶች በማጠቃለል በመግቢያና መውጫ በሮች ለሚገኙ ቅ/ፅ/ቤቶችና ጣቢያዎች በየወሩ ያሰራጫል፡፡

4) በተፈቀደላቸው የጊዜ ገደብ ያልወጡትን ተሽከርካሪዎች በተመለከተ በ10 ቀን ልዩነት ሁኔታውን በማጣራት ለባለሥልጣኑ የህግ ማስከበር ዘርፍ፣ ለክልልና ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን እና ለመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ክትትል እንዲደረግ መረጃ ያስተላልፋል፡፡

5) በዚህ መመሪያ የተመለከቱና ለቱሪስቱ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ድረ ገፅ እንዲካተት ያደርጋል፡፡

6) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሠ) መሰረት የተሽከርካሪው አካል ስለመፈቀዱ ለገባበትና ለሚወጣበት ቅ/ጽ/ቤት ያሳውቃል

## 9. የመረጃ አያያዝ፣ ልውውጥና ስርጭት

1) የጉምሩክ መግቢያና መውጫ በሮች መስተንግዶ ስለተሰጠው ዕቃ የድንበር አስተዳደርና የኮንትሮባንድ ክትትል ዳይሬክቶሬት አዘጋጅቶ በሚልከው ዝርዝር መረጃ መስተንግዶ በተሰጠ በ5 ተከታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ድንበር አስተዳደርና የኮንትሮባንድ ክትትል ዳይሬክቶሬት መተላለፍ ይኖርበታል፡፡

2) የጉምሩክ መግቢያና መውጫ በሮች በዚህ መመሪያ መሰረት መስተንግዶ የሰጡባቸውን የገቢና ወጪ ቀሪ የዕቃ ዲክለራስዮን እየመዘገቡ ፋይል አድርገው ይይዛሉ፡፡

3) የጉምሩክ መግቢያና መውጫ በሮች ለሰጡት አገልግሎት የድንበር አስተዳደርና የኮንትሮባንድ ክትትል ዳይሬክቶሬት አዘጋጅቶ በሚልከው ቅፅ መሠረት በወቅቱ በመመዝገብ ወርሃዊ ማጠቃለያ ሪፓርቱን ወሩ ባለቀ በቀጣይ ሁለት የሥራ ቀናት በፋክስ፣በኢሜልና በአውትሉክ ለድንበር አስተዳደርና የኮንትሮባንድ ክትትል ዳይሬክቶሬት ያስተላልፋሉ፡፡

4) ይህ መመሪያ ተፈፃሚ መሆን ከሚጀምርበት ጊዜ ጀምሮ የሚሰጥ አገልግሎት በእያንዳንዱ የመግቢያ በር የራሱ የሆነ ተከታታይ መለያ ቁጥር ያለው የፈቃድ ወረቀት ይሰጣል፡፡ መለያውም ሦስት ክፍሎች ይኖሩታል እነዚህም፤

ሀ/ የመግቢያ በሩ ስም፤

ለ/ በዓመቱ በመጀመሪያ ለገባው ዕቃ 00001 ጀምሮ እስከ ዓመቱ መጨረሻ ተከታታይ ቁጥር ይሰጣል፡፡

ሐ/ የዲክላራሲዮን መለያ አመዘጋገቡ ቅ/ጽ/ቤቱን የሚገልጽና 0001 ከሚል መነሻ ቁጥር ጀምሮ ዓመተ ምህረቱን የያዘ ይሆናል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ የተዘረዘረው ሥርዓት ቢኖርም የመረጃ ቴክኖሎጂ ሥርዓት በተዘረጋባቸው የጉምሩክ መውጫና መግቢያ በሮች የመረጃ አያያዝ ሪፖርት አቀራረብ በሲስተም አሰራር መሰረት ይሆናል፤ ይህንንም ስርዓት ለመተግበር የመረጃ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ስርዓቱን ያመቻቻል፡፡

6) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 የተቀመጠው የዕቃ ዲክለራስዮን አቀራረብ ስነ-ሥርዓት በባለስልጣኑ ሰራተኞች ይፈጸማል፡፡

## 10. <u>ዋስትና</u>

1) ቱሪስቱ በጊዜያዊነት ይዞት ለሚገባው ዕቃ የቀረጥና ታክሱን መጠን የሚያክል የጥሬ ገንዘብ ተቀማጭ ፣ የባንክ ጋራንቲ ወይም የኢንሹራንስ ቦንድ ዋስትና ማስያዝ ይኖበታል፡፡

2) ለአለም አቀፋዊ ወይም አህጉራዊ ጉባኤ ወይም ስብሰባ የሚሳተፉ ሰዎች በጊዜያዊነት ለሚያስገቡት ፕሮፌሽናል ካሜራ የዋስትና ግዴታውን የሚያቀርበው የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ሲሆን የሚቀርበው የዋስትና አይነትም የጽሁፍ ዋስትና ይሆናል፡፡

3) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 አፈጻጸም የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጽ/ቤት የሚሰጠው የደብዳቤ ዋስትና ይዘት ባለስልጣኑ በሚያዘጋጀው ቅጽ መሰረት ይሆናል ፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ቱሪስቱ በጊዚያዊነት ለሚያስገባው ዕቃራሱ ዕቃውን በዋስትና ማስያዝ ይችላል፡፡

## 11. <u>ቁጥጥርና ክትትል</u>

በመተላለፊያ መስመሮች ላይ የሚገኙ የጉምሩክ ጣቢያዎች በተለያዩ ምክንያቶች ክትትል እንዲደረግባቸው መረጃ በተላለፈባቸው ዕቃዎች ላይ ቁጥጥር በማድረግ መረጃውን ላስተላለፈው ክፍል ወዲያውኑ ውጤቱን ያሳውቃል፤ እንደአስፈላጊነቱም ዕቃውን በአጃቢ ለጠያቂው ክፍል ያስተላልፋል፡፡

## 12. <u>በተወሰነው የጊዜ ገደብ ስላልተመለሰ ወይም ከታለመለት ዓላማ ውጭ ስለዋለ ዕቃ</u>

1) በዚህ መመሪያ መሰረት በጊዜያዊነት አገር ውስጥ የገባ የቱሪስት ዕቃከአገር ውስጥ የሚቆይበት ጊዜ ካልተራዘመ በስተቀር በህግ የተወሰነው የመቆያ ጊዜ እንደተጠናቀቀ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ተመልሶ ካልወጣ በዋስትና የተያዘው ገንዘብ በሙሉ ለመንግስት ገቢ ተደርጎ በእቃዉ ላይ ተገቢው የጉምሩክ ፎርማሊቲ ተከናውኖበት አገር ውስጥ ሊቀር ወይም ከአገር ሊወጣ ይችላል፡፡

2) በዚህ መመሪያ መሰረት በጊዜያዊነት አገር ውስጥ የገባ የቱሪስት ዕቃ ከታለመለት ዓላማ ውጭ የዋለ እንደሆነ በዋስትና የተያዘው ገንዘብ ለመንግስት ገቢ መደረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Revenues and Customs Authority

በዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባውን የቀረጥና ታክስ መጠን 50% መቀጮ ተከፍሎበት ከአገር እንዲወጣ ይደረጋል። ሆኖም በዋስትና የተያዘው እቃው በሚሆንበት ጊዜ ተሸጦ ቀረጥና ታክሱ፣ የቀረጥና ታክሱን 50% መቀጮ እና ዕቃን ለመሸጥ የወጣው ወጭ እንዲከፈል ተደርጎ ቀሪው ለባለቤቱ ተመላሽ ይደረጋል።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርምቱሪስቱ በዋስትና ያስያዘው በጊዜያዊነት የገባውን ዕቃ በሚሆንበት ጊዜ በዋስትና የተያዘው ዕቃ ተሸጦ ቀረጥና ታክሱን እና ዕቃውን ለመሸጥ የወጣው ወጭ ተቀናሽ ተደርጎ ቀሪው ገንዘብ ለባለቤቱ ተመላሽ ይደረጋል።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው ቢኖርም የዕቃው ባለቤት የቀረጥና ታክሱን መጠን የሚያክል ገንዘብ ከፍሎ እቃውን ከአገር ሊያስወጣ ወይም ተገቢውን የጉምሩክ ስነ ስርአት በመፈጸም አገር ውስጥ ሊያስቀር ይችላል።

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 13. የተሻሩህጐች

1) ለቱሪዝምና ለባህል ልውውጥ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 54/2003 በዚህ መመሪያ ተሽሯል።

2) ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማናቸውም መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ መመሪያ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም።

### 14. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በዋና ዳይሬክተሩ ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ 12/09/ቀን 2008ዓ.ም.

አብርሃም ንጉሴ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክባለስልጣን

ተጠባባቂ ዋና ዳይሬክተር

# ቱሪስቶች በጊዜያዊነት ወደ ሀገር የሚያስገቧቸው ዕቃዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ምደባ | የማቴሪያሎች አይነት |
|---|---|---|
| 1. | የካምፕ ማቴሪያሎች | ቀላል ማቴሪያሎች- ሶላር ወይም ቻርጅ የሚደረግ ወይም ባትሪ |
| | | የመሳሪያ ሳጥኖች (ብረት ወይም ፋይበር፣ ትልቅ ወይም ትንሽ ሊሆን ይችላል) |
| | | የፊት ለፊት መብራቶች |
| | | የካምፕ መብራቶች |
| | | የካምፕ ብረቶች፣ ሽራ፣አልጋ ልብሶች |
| | | የመጀመሪያ እርዳታ ድንኳን |
| | | ፍራሽ |
| | | የእንቅልፍ ከረጢቶች |
| | | ትራስ |
| | | ተንቀሳቃሽ መጸዳጃ ቤት |
| | | ተንቀሳቃሽ ሻወር ከረጢት እና ተያያዥነት ያላቸው መሳሪያዎች |
| | | 2 -3 ሊ/ቮልት ጀኔሬተር |
| | | የውሃ ኮንቴነሮች |
| | | ጃንጥላ እና የዝናብ ልብስ |
| 2. | የማድቤት ማቴሪያሎች | ጠረጴዛ |
| | | ወንበር |
| | | ምድጃ |
| | | ሲሊንደር |
| | | የተለያዩ አምፖሎች እና ሳህኖች፣ ዝርግ ሳህኖች እና ተያያዥነት ያላቸው ዕቃዎች |
| | | የተለያዩ የምግብ ዓይነቶች |
| 3. | የአደን ማቴሪያሎች | ጠመንጃ |
| | | ጥይት እና ተያያዥነት ያላቸው መሳሪያዎች |
| 4. | የወፎች መመልከቻ ማቴሪያሎች | ቢኖኩለርስ |
| | | ቴሌስኮፒ |
| 5. | የተራራ መውጫ ማቴሪያሎች | ሄልሜት |
| | | የተለያዩ ኬብሎች |
| | | የተለያዩ ብረት ማቴሪያሎች ማጣበቂያ |
| 6. | የቲሪስ መጓጓቻች | ተይዘው የሚኬዱ ቦቲ ጫማዎች |
| | | ታድ ሌፍት |
| | | ትንሽ የጀልባ ሞተር |
| 7. | ሌሎች | የመራመጃ ማጣበቂያዎች |
| | | ፓራግሊዲንግ ሞተር ጀቶች |
| | | ጀልባዎች |
| | | ተሽከርካሪዎች |
| | | ሞተር ብስክሌቶች እና ሌሎች መለዋወጫ እቃዎች |
| | | የተራራ መውጫ ሞተር ብስክሌቶች እና ተያያዥነት ያላቸው መለዋወጫ ዕቃዎች |
| | | መድሃኒቶች |
| | | የጽሁፍ መሳሪያዎች |
| | | የተለያዩ የፎቶ እና የቪዲዮ ካሜራዎች እና ተጓዳኞቻቸው |
| | | ሄልኬም ካሜራ |
| | | ባለ ሶስት እግር ለካሜራዎች እና ቴሌስኮፒዎች |
| | | ወኪቶኪ እና ገመድ አልባ ስልኮች እና ተያያዥነት ያላቸው መሳሪያዎች |

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Revenues and Customs Authority